# የኮሚቴ ቱሪስቶች እና ታርጋቸው

ከመላኩ ይስማው

አንዳንድ ቃላት አሉ የሚያሳዝኑኝ። ባንዳንድ ሰዎች ትርጉማቸው ተጣሞ ዘወትር ግልጋሎት ላይ የሚውሉ። “ሀገር ወዳድ”፣ “ገለልተኛ” ወዘተ የሚሉት ዓይነት። በ የአካባቢያችሁ ቃላቱን አዘውትረው የሚጠቀሙትን ሰዎች ልብ ብላችሁ ላፍታ አጢኑ። መድረክ ይወዳሉ። ወደ አካባቢው ብቅ ያለ ማንኛውም ተቃዋሚ ድርጅት ወይም እንቅስቃሴ መሪ ሁሉ ግንባር ቀደም አስተናጋጅ ናቸው። በሚቋቋመው የድጋፍ ኮሚቴ ሁሉ መግባት ያዘወትራሉ። የጋዜጠኞች፣ የመምህራን፣ የሰብዓዊ መብት፣ የድንበር ጉዳይ፣ ወዘተ የድጋፍ ኮሚቴ --- የማይገቡበት የለም።

በወያኔ የይስሙላ ፓርላማ ተመጥኖ የሚሰጥ ወንበርን አንቀበልም፣ የህዝብ ድምፅ ይከበር!! --- መፈክር። ያጨበጭባሉ፣ ያስጨበጭባሉ። ወያኔን እስከወዳኛው በትጥቅ/በሁለገብ ትግል አስወግዶ፣ የህዝብ የስልጣን ባለቤትነት ማርጋገጥ!! --- አሁንም መፈክር። ያጨበጭባሉ፣ ያስጨበጭባሉ። በግልብጡም ከወያኔ ጋር ተለሳልሶ፣ የሚቀማውን የህዝብ ድምፅ ቀምቶ እየመጠነ የሚሰጠውን የይስሙላ ፓርላማ ወንበር በመቀበል በጊዜ ብዛት እንደምናሸንፈው ተስፋ እናደርጋለን!! --- ፀሎት አይሉት መፈክር። ያጨበጭባሉ፣ ያስጨበጭባሉ። የመፈክር ማዕድ ቤት ወጥ ቀማሾች። መፈክሩን የሚያዘጋጅላቸው ሰው ትላንት ምን ይል ነበር? ነገስ ምን ሊል ሰንቆልናል? እስከ መቼስ በፅናት ይመራናል? ብለው መጠየቅ ጋር የሚተዋወቁ አይመስልም። ለነገሩ እነሱም የሚሰጡት ድጋፍ ሌላ አጀንዳ አስያዥ ባካባቢያቸው ጎራ እስከሚል ነው።

ባካባቢያቸው የሚመሰረተው ኮሚቴ ሁሉ እፍታ ቀማሾች ናቸው። የመጣ “ተቃዋሚ” ነኝ ባይ ሁሉ መፈክር አስተጋቢ ማሚቶዎች ናቸው። አንዱን ይጀምሩትና ከተወጠነው ያጭርም ይሁን የረጅም ጊዜ እቅድ አንዱም ሳይሳካ፣ ሌላ አካባቢያቸውን ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ የሚመለከት እንቅስቃሴ ከተጀመረ ጥልቅ ነው። የኮሚቴ ቱሪስቶች።

ታዲያ ይህ የኮሚቴ ቱሪስትነታቸውን ትክክለኝነት ለማስረገጥ/ለማሳመን ከሚጠቀሙባቸው ሐረጋት አንዱ “ሀገር ወዳድ” ነኝ የሚል ነው። ሀገርና ሕዝብን ይታደጋል ብለው የሚያምኑበት የፖለቲካ ድርጅት ወይም ሕዝባዊ ማህበር በመግባት ፀንቶ እና ቆርጦ መታገል “ሀገርን መጥላት” የሆነ ይመሰል። የኢትዮጵያን አንድነት እና የህዝቧን የዴሞክራሲ መብት ጥያቄ ማስከበር ዓላማቸው ካደረጉት የፖለቲካ ድርጅቶች ወይም የሲቪክ እንቅስቃሴ በአንዱ ሲሳተፉ/እየተሳተፉ ግንባራቸውን ለጥይት፣ አካላቸውን ለስቃይ የሰጡ/የሚሰጡ ወገኖችስ ሀገር የጠሉ ናቸውን? ስለሀገርና ስለህዝብ ዋጋ መክፈላቸው የፍቅራቸው ማስረገጫ መሆን ያንሰዋልን?

እነኚህ ባለ “ሀገር ወዳድ” ታርጋዎች ሌላም የሚያዘወትሩት ሐረግ አለ። “እኔ ገለልተኛ ነኝ፤ ከወያኔ ሌላ የማየው ጠላት የለኝም” የሚል። ይህ መቼም የወያኔንና አጋሮቹን የጥቃት ተንኮልና እና አመጣጥ በወጉ አለመገንዘብ፤ አለዚያም አጉል ስሜታዊ የሆነ ጥሬነት ይመስለኛል። የህዝብ ወገን ነን የሚሉ ሁሉ ወያኔ በግልፅም በስውርም ሊያጠቃቸው እንደሚያደባ መገንዘባቸው የትግሉ ሀ ሁ ነው ባይ ነኝ። ባጠፌታውም በሚያመቻቸው መንገድ ሁሉ ወያኔን ማጥቃት፤ እራሳቸውንም መከላከል የግድ ይሆናል። ወያኔ ሁሉጊዜም ወያኔ ነኝ ብሎ ያጠቃኛል ብሎ የሚያስብ ካለ የዋህ ነው። ቢያንስ ቢያንስ ከእነ ልዴቱ እና መሰሎቹ ያልተማረ። ካልሆነም ከወያኔ ወይም ከሕዝብ መቁረጥ ያቃተው ወላዋይ ወይም ወያኔ ተከል (አስመሳይ) ነው።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እነኝህ የኮሚቴ ቱሪስቶች እና ባለቃላት ታርጋዎች በየአካባቢያቸው የኢትዮጵያዊውን ማህበረሰብ የጋራ እንቅስቃሴ እንደ ውሃ ያዋልሉታል። በየጊዜው ወያኔ ወይም አቅጣጫ አስቀያሪ ተቀፅላዎቹ ወይም አትራፊ ነጋደዎች የሚፈጥሯቸውን አጀንዳዎች ተከትለው ኮሚቴ በመፈልፈል፤ የወገንን እንቅስቃሴ ግብ ያልሰነቀ፣ ወያኔም ላይ ዒላማውን ያላነጣጠረ ያደርጉታል። ትግሉን በማጠናከር ፈንታ ያዳክሙታል። ባጭሩ ከወያኔ ጋር የሚካሄደውን ትግል ከውዥንብር እና ከማወላወል የፀዳ፣ ግልፅነትና ቁርጠኝነትን የተላበሰ መሆን ቢገባውም መስመሩን እያሳቱ ባለበት ያሳረግጡታል ወይም ወደሁዋላ ይመልሱታል።

በሚምሉበት የህዝብ ትግል ላይ እያደረሱ ያለውን ጥፋት መቼ ይሆን ቆም ብለው የሚያገናዝቡት? ጤነኛ ልቦና ካላቸው። ካልሆነም መቼ ይሆን ሰው የሚመክራቸው? እገሌን አምነዋለሁ ወይም አምናታለሁ የሚል ሳይሆን ትላንትን፣ ዛሬ እና ነገን አስተውሎና አገናዝቦ ድክመታቸውን የሚነግራቸው ወዳጅ በዙሪያቸው ካለ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com